# RAINIER BEACH: A BEAUTIFUL SAFE PLACE FOR YOUTH (ለወጣቶች የሚስማማ ውብና አስተማማኝ ቦታ)

## የፕሮጀክትና የግምገማ ማጠቃለያ

Charlotte Gill, Zoe Vitter, እና David Weisburd
Center for Evidence-Based Crime Policy, Department of Criminology, Law & Society, George Mason University (በጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርሲቲ፣ የክሪሚኖሎጂ፣ ሕግና ማሕበረሰብ ትምህርት ክፍል፣ የማስረጃ ተኮር ወንጀል ፖሊሲ ማዕከል)

## RAINIER BEACH ምንድን ነው፡ A BEAUTIFUL SAFE PLACE FOR YOUTH?

Rainier Beach: A Beautiful Safe Place for Youth (ABSPY) ማሕበረሰብ መር ቦታ ተኮር የሆነ የጥቃት መከላከያ ፈጠራዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የፕሮግራሙ ግብ በ Rainier Beach መኖሪያ አካባቢ የወጣቶችን ሰለባነትና የወንጀል ተሳትፎ መቀነስ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ስያሜውን ያገኘው የ Rainier Beach ማሕበረሰብ በ Neighborhood Plan Update ውስጥ ካስቀመጠው ራዕይ በመነሳት ሲሆን ይህም ራዕይ Rainier Beach ውብና አስተማማኝ ቦታ ማድረግ ነው፡፡ ABSPY በመኖሪያ አካባቢ ውስጥ በሚገኙ አምስት አነስተኛ የጎዳና ብሎኮች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው —"ቁልፍ ቦታዎች"—በ2012 Rainier Beach ውስጥ የወጣቶች ተሳትፎ ካለባቸው የወንጀል ክስተቶች ውስጥ ግማሽ ያህሉ የተፈጸሙት በእነዚህ ቦታዎች ነው፡፡ አምስቱ ቁልፍ ቦታዎችም፡ Rose Street, Rainier and Henderson, Rainier Beach Light Rail Station, Lake Washington, እና Our Safe Way ናቸው፡፡

## የፕሮጀክት ዳራ

ABSPY በተለያዩ የምርምር ጥናቶች ላይ የተመሰረተ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ከሲያትል በ David Weisburd እና ጓደኞቹ የተደረገው ጥናት አንዱ ሲሆን ይህም ጥናት ያሳየው ውጤት በከተሞች ውስጥ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች መካከል ግማሽ የሚሆኑት የሚመነጩት በጣም አነስተኛ ቁጥር ካላቸው፣ ማለትም ከጎዳና ብሎኮች ውስጥ 5 በመቶ ከሚሆኑት እንደሆነ ነው፡፡ ወጣቶችን የሚያሳትፍ ወንጀል ደግሞ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆኑ ቦታዎች እንደሚነጭ ይጠበቃል፤ የዚህ ምክንያት ደግሞ ወጣቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት እንደ ት/ቤት፣ ፓርክና ሌሎች ሕዝባዊ ቦታዎች በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ፣ በእንደዚህ ዓይነት ቦታዎች የወጣቶች ወንጀል ተሳትፎ ይጨምራል፡፡ አንድ ጥናት እንዳሳየው ከሆነ ፖሊሶች ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች ላይ በሚያደርጉት ወረራና የማሰር ተግባር ወንጀልን በመቀነስ ረገድ ውጤታማ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እስራትና ክስ የመመስረት እርምጃ ለወንጀል የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ በሆኑ ወጣቶች ዘንድ ቅሬታን ይፈጥራል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ABSPY የሚያተኩረው ከእስራት ውጭ ባሉ ወንጀልን የመቀነሻ ስልቶች ላይ ሲሆን ከእነዚህ ስልቶች መካከልም የማሕበረሰብ አመራርና ብቃትን በማጎልበት ችግሮችን መፍታትና ለወንጀል የሚገፋፉ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመቅረፍ የማሕበረሰቡን ደህንነት ማጎልበት ነው፡፡

## የፕሮጀክት አመራርና ድጋፍ

ABSPY የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ2012 ከ Byrne Criminal Justice Innovation Program (ባይርን ክሪሚናል ጀስቲስ ኢኖቬሽን ፕሮግራም) በተሰጠ የ$1 ሚሊዮን ድጋፍ ከተገኘ በኋላ ነበር፡፡ ይህ ፕሮግራም በ U.S. Department of Justice's Bureau of Justice Assistance (ዩኤስ የፍትሕ ሚኒስቴር የፍትሕ ድጋፍ ቢሮ) የሚመራ ነው፡፡ Byrne Criminal Justice Innovation Program በከተሞች፣ ማሕበረሰቦችና ተመራማሪዎች መካከል አጋርነትን በመደገፍ ማሕበረሰብ መር፣ ቦታ ተኮርና በመረጃ የታገዘ የችግር አፈታት ዘዴዎችን ለመቅረጽ ያግዛል፡፡ ABSPY ከሲያትል ከተማ፣ ከ Seattle Neighborhood Group (ሲያትል ኔይበርሁድ ግሩፕ)፣ ከ Seattle Police Department (ሲያትል ፖሊስ መምሪያ) ከ Boys and Girls Club of King County (የኪንግ ካውንቲ ወንዶችና ሴቶች ክለብ) እና ከ Rainier Beach Action Coalition (ከRainier Beach አክሽን ጥምረት) የተውጣጡ ተወካዮችን ከያዘ ቡድን

የምክር አገልግሎት ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ABSPY ለየት የሚያደርገው  በአካባቢው የሚከሰቱ ወጣቶችን የሚያሳትፉ የወንጀል ድርጊቶችን ዋነኛ መንስኤ ለመቅረፍ የሚያስችሉ ማስረጃ ተኮር ስልቶችን በመቀየስ ረገድ የመሪነት ሚናውን የሚጫወት መሆኑ ነው፡፡

## ማሕበረሰብ መር ችግር አፈታት

የ ABSPY አቀራረብ በዋነኛነት የተመሰረተው በ Community Task Force (CTF፣ የማሕበረሰብ ግብረ ኃይል) በማቋቋም ላይ ሲሆን ይህ ግብረ ኃይል የ Rainier Beach መኖሪያ አካባቢን ብዝኃዊነት የሚያንጸባርቁ ቁጥራቸው ከ100 የሚበልጡ የማሕበረሰብ አባላትን ያቀፈ ነው፡፡ ከ City of Seattle’s Public Outreach and Engagement Liaisons (የሲያትል ከተማ የሕዝብ አውትሪችና ተሳትፎ አገናኝ ጽ/ቤት) በተገኘ ድጋፍ አማካይነት ይህ ቡድን የተመለመለው በቀጥታ ከአምስቱ ቁልፍ ቦታዎች ሲሆን በውስጡም ነዋሪዎችን፣ የንግድ ሥራ ባለቤቶች፣ ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ከእነዚህ ቦታዎች ጋር ትስስር ያላቸውን ሌሎች አካላት ያቀፈ ነው፡፡ የ ABSPY ዋና ቡድን ከ Community Anti-Drug Coalitions of America (CADCA, የአሜሪካ የማሕበረሰብ ፀረ-አደንዛዥ ዕፅ ጥምረቶች) ጋር በመተባበር ኦክቶበር 2013 ላይ የአንድ ቀን ሥልጠና አዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን በሥልጠናውም CTF በአካባቢያቸው ከሚያገኙት መረጃ፣ ከማሕበረሰብ ተሞክሮና ከምርምር ማስረጃ በመነሳት ችግሮችንና የስጋት ምንጮችን እና ለወንጀል መፍትሄ የሚሆኑ ከማህበረሰብ ጤና መስክ ስልታዊ የሆነ የማህበረሰብ ችግር አፈታት እንዴት ማወቅ እንደሚችሉ ተምረዋል፡፡ ከሥልጠናው በማስከተልም ስድስት ተከታታይ ወርክሾፖች የተዘጋጁ ሲሆን CTF በአምስት ቡድን ተከፋፍለው፣ ማለትም ለአንድ ቁልፍ ቦታ አንድ ቡድን ተመድቦ ለእያንዳንዱ ቁልፍ ቦታ ተጨባጭ ሁኔታ የሚስማሙ እርምጃዎችን ቀይሰዋል፡፡ እነዚህ እርምጃዎችም በአራት አበይት መስኮች ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡

1. ቁጥጥርን መጨመር እና ለወጣቶች መዋቅርን መስጠት
2. አካባቢን መቀየር
3. ፖሊሲዎችንና ህጎችን መቀየር
4. የጋራ ብቃትን (“አካባቢን ይወስዳል“) መንፈስን መገንባት

በ CTF ወርክሾፖች አማካይነት የማሕበረሰብ አባላት በእያንዳንዱ አካባቢ የሚፈጸሙ ወጣቶችን የሚያሳትፉ የወንጀል ድርጊቶችን በተመለከተ “ታሪክ እንዲናገሩ” የተጠየቁ ሲሆን በችግሮች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ገልጸው በእያንዳንዱ ቦታ ያሉትን የስጋት መንስኤዎችም ለይተዋል፤ ይህን ሲያደርጉም ተፈላጊ ውጤቶችን ታሳቢ አድርገዋል፣ በጥናት ማስረጃ የተደገፉ የመፍትሔ ሃሳቦችን አቅርበዋል፣ የእያንዳንዱን አቀራረብ አዋጭነትም መዝነዋል፡፡ ወርክሾፖቹ ሲጠናቀቁም የተጠቆሙት የእርምጃ ሃሳቦች “The Gathering” ተብሎ በሚታወቅ አሳታፊ ፕሮግራም ላይ ለ Rainier Beach ማህበረሰብ ቀርበዋል፡፡

## የመፍትሔ እርምጃዎች

ዋና ቡድንና የ CTF ስራ በአምስቱ ቁልፍ ቦታዎች በተለዩት ወጣቶችን በሚያሳትፉ የወንጀል ድርጊቶች የስጋት መንስኤን በቀጥታ የሚቀርፍ የትግበራ እቅድ እንዲቀረጽ ያስቻለ ሲሆን የተለያዩ የከተማና የማሕበረሰብ አጋሮችን ሙያዊ ክህሎትም ያካተተ ነበር፡፡ በእቅዱ ውስጥ የተጠቆመው እያንዳንዱ እርምጃ ከላይ ከተጠቀሱት የትኩረት መስኮች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሚመለከት ነበር፡፡ በሌሎች የመፍትሔ እርምጃዎች የሚታገዝና የሚዳብር ሲሆን የእያንዳንዱን ቦታ ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባትም በተወሰኑት ወይም በሁሉም ቁልፍ ቦታዎች ላይ እንዲተገበር የታቀደ ነበር፡፡

አብዛኞቹ የተጠቆሙ የመፍትሔ እርምጃዎች ያተኮሩት በ Rainier Beach ውስጥ የሚገኙ የማሕበረሰብ አባላትን በማሳተፍ በጎረቤታሞች መካከል ያሉ እንቅፋቶችን በመስበር ግንኙነቶችና የችግር አፈታት አቅምን መገንባት ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሃሳቦች የተገኙት ከ CTF ግኝቶች ሲሆን አንዳንድ የማሕበረሰብ አባላት እርስ በእርሳቸው፣ በተለይ ደግሞ ከወጣቶች ጋር ለመነጋገር የሚፈሩ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ከ2014 የበጋ ወቅት ጀምሮ፣ በማሕበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ የ **Corner Greeter** ፕሮግራሞች የተካሄዱ ሲሆን በወቅቱም የማነቃቂያ ምግብና መጠጥና የመዝናኛ ዝግጅቶች በእያንዳንዱ ቁልፍ ቦታ ላይ ተመቻችተው ስለነበር በወቅቱም ማሕበረሰቡን ለማሳተፍና ቀደም ሲል አደገኛ ተደርገው የሚቆጠሩ ቦታዎችን “ለማነቃቃት” አስችሏል፡፡ በፕሮጀክቱ ዘመን በማሕበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ተግባራትና ዝግጅቶች የተካሄዱ ሲሆን አብዛኞቹም የታቀዱት በወጣቶች እና እንደ Rainier Beach Action Coalition ካሉ የማሕበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ነው፡፡ የእነዚህ የጎረቤት እና የወጣቶች ተሳትፎ ተግባራት ግብ ቁልፍ ቦታዎችን ወደ ጤናማ አካባቢ “በመቀየር” ወጣቶች በማሕበረሰቡ ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡

አነስተኛና በአካባቢው ሰው ባለቤትነት የሚተዳደሩ የንግድ ተቋማት ለ Rainier Beach በጣም ወሳኝ ናቸው፡፡ ሌሎቹ የመፍትሔ እርምጃዎች ያተኮሩት ደግሞ በ **ንግድ ሥራ ተሳትፎ** ላይ ነው፡፡ የንግድ ሥራ ተሳፎ አስተባባሪ የ Seattle Neighborhood Group ሲሆን ከ Rainier Beach Merchants Association (Rainier Beach የነጋዴዎች ማሕበር)፣ ከ Seattle Police Department (ሲያትል ፖሊስ መምሪያ)፣ ከአካባቢያዊ የማሕበረሰብና የኢኮኖሚ ልማት ድርጅቶች ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ የንግድ ሥራ ተሳትፎ ዓላማ

በአካባቢው የሚገኙ የንግድ ተቋማት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለማወቅ፣ በንግድ ስራ ተቋማት መካከል እና ፖሊስ ጋር ያለ ግንኙነትን ማዳበር፣ የንግድ ሥራ ባለቤቶች ወንጀልን የመከላከልና ሪፖርት የማድረግ ችሎታቸውን ማሳደግ ነው፡፡ **Crime Prevention Through Environmental Design (CPTED, በአካባቢያዊ ዲዛይን አማካይነት ወንጀልን መከላከል)** የተባሉ የመፍትሔ እርምጃዎችና ግብዓቶች ዲዛይን፣ ንድፍና የቦታ አያያዝን ለማሻሻል ሲባል ለንግድ ሥራ ተቋማት ቀርቦላቸዋል፡፡

በ Rainier and Henderson የሚገኘው የ Rainier Beach ካምፓስ አራት ት/ቤቶች የሚገኙበት ሲሆን የማሕበረሰቡ ማዕከል ነው፡ ፡ ABSPY ዋነኛ ባለድርሻ አካላትን በማሰባሰብ የ **Rainier Beach Campus Safety Team (የ Rainier Beach ካምፓስ የደህንነት ቡድን**) የመሰረተ ሲሆን በዚህ ቡድን አማካይነት የከተማውና የሲያትል የሕዝብ ት/ቤቶች ከማሕበረሰብ አጋሮች ጋር በመተባበር ደህንነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ሃሳቦችን ለማዳበር ይሰራል፤ ለምሳሌም ተማሪዎች ከት/ቤት የሚለቀቁበትን ሰዓት በማሻሻል በርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች በቁልፍ ቦታዎቹ ላይ እንዳይከማቹ መከላከል ይገኙበታል፡፡ የ Rainier Beach Campus የመፍትሔ ሃሳቦች ዋነኛ ትኩረት የነበረው የ **Safe Passage** ፕሮግራም ሲሆን የሚመራውም በ Boys and Girls Club of King County (የኪንግ ካውንቲ ወንዶችና ሴቶች ክለብ) ነው፡፡ የ Safe Passage ቡድን ወጣቶች ከት/ቤት በሚለቀቁበት ወቅት የእንክብካቤ፣ የቁጥጥርና የማበረታቻ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የቡድኑ አባላት በላዩ ላይ “Be Safe” የሚል ጽሁፍ የታተመበት ደማቅ ሰማያዊ ቲሸርት በመልበስ በግልጽ የሚታዩ ድጋፍ ሰጪ ጎልማሶችና ተምሳሌቶች ሆነው ነበር፡፡

## የግምገማ ግኝቶች

The Center for Evidence-Based Crime Policy at George Mason University (በጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርሲቲ የማስረጃ ተኮር ወንጀል ፖሊሲ ማዕከል) በፕሮጀክቱ ዕድሜ የምርምርና የግምገማ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የፕሮግራሙን ውጤታማነት ለመመዘን እንዲቻል ከሴፕቴምበር 2011 እስከ ኦገስት 2016 ድረስ ከአምስቱ ቁልፍ ቦታዎች የፖሊስ አገልግሎት ለማግኘት የተደረጉ የስልክ ጥሪዎችንና ሪፖርት የተደረጉ ወንጀሎችን ተከታትለናል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱን ቁልፍ ቦታ ከማነጻጸሪያ ቁልፍ ቦታ ጋር ማለትም በሲያትል የፖሊስ መምሪያ የደቡብ ቀጠና ክልል ውስጥ ከሚገኝ ተመሳሳይ ቦታ ጋር አዛምደናል፡፡ ከዚህም ሌላ በ Rainier Beach መኖሪያ አካባቢ ያለውን የወንጀል መጠን በደቡብ ቀጠና ካለው አጠቃላይ አዝማሚያ ጋር በማነጻጸር መዝነናል፡፡ በቁልፍ ቦታዎችና በማነጻጸሪያ ቦታዎች ላይም ሁለት የማሕበረሰብ ዳሰሳ ጥናቶችን አድርገናል ነበር፡፡ አንዱ የተካሄደው የመፍትሔ እርምጃዎቹ ከመጀመራቸው በፊት በ2014 በጋ ወቅት ሲሆን ቀጣዩ ደግሞ በ2016 በጋ ወቅት የተደረገ ነበር::

ግኝታችን የሚያሳየው፡

- ቁልፍ ቦታዎች በጊዜ ሂደት ቁልፍ ቦታነታቸው መቀነሱን፡፡
- በ South Precinct የሚሰሩ ወንጀሎች በአጠቃላይ መቀነሳቸውንና ከከተማው አንጻር መቀነሱን፡፡
- ከ South Precinct አጠቃላይ አካባቢ ይልቅ በቁልፍ ቦታዎች ከባባድ ወንጀሎች ቀንሰው ታይተዋል፡፡
- በአንዳንዶቸ ቁልፍ ቦታዎች ለአገልግሎት፣ የፖሊሰ እንቅስቃሴ እና የተጠቆሙ ክሰተቶች ቁጥር ጨምሯል፡፡ ይህ የስጋት ምንጭ አይሆንም - ሊያሳይ የሚችለው ABSPY ግቡን እንደመታና የአካባው ነዋሪዎች ተሳትፎ መጨመሩን እዲሁም በፖሊስ ላይ ያለ እምነት መጨመሩን፡፡
- በ ABSPY ቁልፍ ቦታዎች በባለፈው አመት የወንጀል ቁጥር እንደቀነሰ የታናገሩ ዳሰሳ የወሰዱ ሰዎች ቁጥር በ 2016 ዳሰሳው ጨምሯል፡፡
- ABSPY በጣም ጠንካራ ያልሆነ ግን ትልቅ አቅም ያለው የሰዎች እይታ እና አጠቃላይ ውጤት እና ችግር እና ስለፖሊስ ያላቸው አመለካከት ላይ ያላቸውን እይታ የሚሻሻል ነው፡፡

በወንጀል ላይ ስታትስተካዊ የሆነ ከግምት ውስጥ የሚገባ መቀነስን አላገኘንም፣ ጣልቃ የመግባት ሂደቱ ሙሉ በሙሉ የተተገበረው ከ ጁን 2016 በኋላ ነው ምክንያቱም አዲስ ፈጠራ የሆነውን፣ ማህበረሰቡን ያማከለውን ስልጥ መተግበር ውስብስብ ስለሆነ ነው፡፡ የወንጀል መቀነስ ውጤትን ለማየት ጊዜ ሊፈጅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ኮሚዩኒቲስ ዛት ኬር የሚባለው፣ የማህበረሰብን ችግር የሚፈታ ፕሮግራም ከተተገበረ በኋላ ስታትስቲካዊ ከግምት ውስጥ የሚገባ ለውጥ ለማምጣት ሶስት አመት ፈጅቷል፡፡

## ጥረትን ማስቀጠል

ቦታዎችና ማሕበረሰቦችን መቀየር ረዥም ጊዜ የሚወስድ ጥረት ነው፡፡ የግምገማ ውጤቶቻችን ተስፋ ሰጪ ጅምር አሳይተዋል፤ በተለይም በችግር አፈታት ሂደትና በትግበራ ወቅት የታየው የማሕበረሰብ ተሳትፎና የ ABSPY የመፍትሔ እርምጃ ተግባራትን እንደ ንግድ ማህበረሰብና ት/ቤቶች ካሉ ሌሎች የአካባቢ ባለድርሻ አካላት ጋር ለማቀናጀት የሚያስችል ማዕቀፍ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ለወጣቶች ውብና አስተማማኝ ቦታ መሆኑን ለመቀጠል እንዲችል ተጨማሪ ስራዎች መሰራት አለባቸው፡፡ ማህበረሰቡን ለማሳተፍ የሚደረጉ ጥረቶች፣ ለምሳሌ የ Corner Greeters ኢኒሺየቲቭ፣ የቢዝነስ ተሳትፎ፣ እና Safe Passage በቁልፍ ቦታዎች ላይ እየተተገበሩ ሲሆን ወጪያቸው ከመንግስት የሚሸፈን በርካታ ትላልቅ የ CPTED streetscape ስራዎች በ2017 መግቢያ ላይ ይከናወናሉ፡፡ ABSPY

አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት በአቅም ግንባታ ረገድ ስኬታማ ስለነበር በዚህም ምክንያት ማሕበረሰቡና ዋናው ቡድን በ2015 ተቀናጅተው ለ2016 ከሲያትል ከተማ ድጋፍ ለማግኘት ችለዋል፡፡ ከተማው ABPSYን እስከ 2018 ድረስ ሙሉ ለሙሉ ድጎማ ተደርጎለታል፡፡ ABSPY ከበርካታ ተሳታፊ ድርጅቶች የዓይነት ልገሳዎችንና ድጋፎችን በማግኘት ለመቀጠል ችሏል፡፡ የመጀመሪያው ስኬታችንም ከዚህ ጋር ለተያያዙ የወጪ አሸፋፈንና ምርምር ስራ አዳዲስ አጋጣሚዎችን የከፈተ ሲሆን ከዚህ መካከል National Institute of Justice (ብሔራዊ የፍትህ ኢንስትቲዩት) በ Rainier Beach ካምፓስና በአጠቃላይ ማሕበረሰቡ ውስጥ አዎንታዊ የባህርይ እርምጃዎችንና ድጋፎችን፣ እንደዚሁም ከቅጣት ይልቅ እርምት ላይ የሚያተኩር ስርዓትን ለማጎልበት የሰጠው $3.8 ሚሊዮን ይገኝበታል፡፡ የሲያትል ፖሊስ መምሪያ ቁልፍ ቦታዎችን ለመለየትና ከማሕበረሰቡ ጋር አብሮ በመስራት ችግርን የመፍታት አቅማቸውን ለመገንባት አብረን ስርተናል፡፡ ABSPY በ Rainier Beach ማሕበረሰብ ውስጥ መሰረቱን በደንብ የዘረጋ ሲሆን ቡድኑም የወደፊት ውጤቶችና ጠቀሜታዎችን ይከታተላል፡፡